# ክትባቶች ከCOVID 19 ይጠብቁናል

## ክትባቱን ማን ሊያገኝ ይችላል?



- ቤት የሌላቸው ሰዎች እና አገልግሎት ሰጭዎች አሁን ክትባቱን መቀበል ይችላሉ ፡፡
- ክትባቱ ለሁሉም ሰው ነፃ ነው ፡፡
- መታወቂያ ወይም ኢንሹራንስ አያስፈልግም ፡፡
- የኢምግሬሽን ወይም የዜግነት ሁኔታ አይወስንም፡፡

## ክትባቱን ለምን መውሰድ ያስፈልጋል?

ማህበረሰብዎን ፣ ወዳጆችዎን፣ ታላቆችን እና እራስዎን በ COVID-19 እንዳይታመሙ ለመጠበቅ ፡፡




ክትባት መውሰድ ወይም አለመውሰድ የእርስዎ ምርጫ ነው፡፡

## እንዴት ነው የሚሰራው?

ክትባቱ ሰውነትዎን ከ COVID-19 ራሱን መከላከል እንዲችል ያስተምራል



ክትባቱ በውስጡ COVID-19 ቫይረስ የለውም ስለሆነም እርስዎ COVID-19ን ሊሰጥዎ አይችልም፡፡

የአሳማ ሥጋ ወይም እንቁላልም የለውም ፡፡

አንዳንድ ክትባቶች ሁለት ጊዜ የሚወሰዱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ አንድ ጊዜ ይወሰዳሉ ፡፡



## ክትባቱ አስተማማኝ ነው?

- ✓ አዎ. እያንዳንዱ ክትባት የተለያየ ዕድሜ ፣ ዘር ፣ የሰውነት ዓይነትና የጤና ሁኔታ ላይ ለሚገኙ አስተማማኝና ውጤታማ ነው ፡፡
- ✓ እያንዳንዱ የ COVID-19 ክትባት በሃኪሞች እና በጤና ባለሙያዎች ደህና ስለመሆኑ ብዙ እርምጃዎችን አልፏል፡፡

# ክትባቶች ከCOVID 19 ይጠብቁናል

## ክትባቱን ስወስድ ምን ይሆናል?

የጤና ባለሙያ ጥቂት ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል ፣ ከዚያ <u>በላይኛው ክንድዎ</u> ውስጥ ክትባቱን ይሰጥዎታል።



ሌላ የጤና ባለሙያ ከ 15 እስከ 30 ደቂቃ ድረስ ከእርስዎ ጋር በመቆየት፣ ማንኛውንም ጥያቄ ሊመልስልዎት ይችላሉ።



## ክትባቱን ከወሰድኩ በኋላ ምን ይሆናል?

- አንዳንድ ሰዎች ክንዳቸውን ሊያማቸው ፣ ራስ ምታት ወይም የድካም ስሜት ሊሰማቸው ይችላል ። ይህ የተለመደ ስለሆነ ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ ያልፋል ።
- ብዙ ውሃ መጠጣት፣ ሙቀትን መጠበቅ ፣ እረፍት ማድረግ ያስታውሱ።
- ከመጨረሻው መጠንዎ ከሁለት ሳምንት በኋላ ሙሉ በሙሉ የክትባቱን ጥበቃ ይሰጡዎታል ።

## ከተከተብኩ በኋላ ምን ማድረግ አለብኝ?



የፊት ሽፋን (ማስክ) ያድርጉ




ከሌሎች ስድስት ጫማ ይራቁ




እጅዎን ብዙ ጊዜ ይታጠቡ

## ጥያቄዎች አሉዎት?

- ኤቨርን ግሪን ሄልዝ የጤና መስመርን በ 425.899.3000 ይደውሉ ፣ ከዚያ 2 ን ይጫኑ ።
- ለበለጠ መረጃ kingcounty.gov/vaccine ይጎብኙ
- የክትባት ቀጠሮ ለመያዝ ፣ 206-477-3977 ይደውሉ (8am-7pm, የቋንቋ አገልግሎቶች ይገኛሉ)



Public Health
Seattle & King County
April 14, 2021